# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት


**መጋቢት / 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

ማውጫ ........ I
የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ ........ I
(EXECUTIVE SUMMERY) ........ I
ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን እና አመሰራረት ........ 1
የኮርፖሬሽኑ ራዕይ እና ተልዕኮ ........ 1
የኮርፖሬሽኑ ስልጣንና ተግባር ........ 2
የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ዘርፍ/አለ በጅምላ/ ተግባርና ኃላፊነት፡- ........ 3
ፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 3
ድርጅታዊ /የዘርፉ/ መዋቅር ........ 3
የፋይናንስ ምንጭ ........ 4
የኦዲቱ ዓላማ ........ 4
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 4
የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ........ 4
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ........ 5
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (EVALUATIVE CRITERIA) ........ 5
ክፍል ሁለት ........ 6
የኦዲት ግኝቶች ........ 6
የኮርፖሬሽኑ የፋይናነስ አስተዳደርን (Financial Managmnet) በተመለከተ፣ ........ 6
የፍጆታ ዕቃዎች  የግዥ ዘዴን በተመለከተ፣ ........ 8
ጥራትን መሠረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ማከናወኑን በተመለከተ ........ 11
ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ ........ 14
ዕቃዎች ደረጃውን በጠበቀ መጋዘን ውስጥ እንዲከማቹ ማድረግን በተመለከተ ........ 15
የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎችን በተመለከተ ........ 17
የፍጆታ ዕቃዎች ክምችትን በተመለከተ ........ 19

የገበያ ጥናት መካሄድን  በተመለከተ ........ 20

የሰው ኃይል አደረጃጀትና የስራ መዘርዝር በተመለከተ ........ 22

የቅሬታ አቀባበል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ ........ 24

ዘመናዊ የመረጃ አያያዝን በተመለከተ ........ 25

ንብረት አያያዝን በተመለከተ ........ 26

ክፍል ሦስት ........ 28

የመደምደሚያ ሃሳቦች ........ 28

ክፍል አራት ........ 30

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 30

አባሪ 1፡ በናሙና የታዩ ........ 33

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 34

አባሪ 3፡ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ/ አለ በጅምላ/ድርጅታዊ መዋቅር ........ 42

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ

## (Executive Summery)

በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን ፤ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ለማረጋገጥ የክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማኑዋል ( Ethiopian Performance Aoudit Manuwal) እና  የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2008 እስከ ጥር 2011 በጀት ዓመት ድረስ ያሉ የስራ ክንውኖችን ነው፡፡

በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን አስቀምጠናል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ  ከቀድሞው አለ በጅምላ ከመጣ ብድር የተነሳ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ውስጥ መሆኑ ፣ ከፍተኛ ዕዳና ወለድ እየከፈለ የሚገኝ መሆኑ እና ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመስራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን ግዥ በዋጋ ማቅረቢያ ብቻ የሚፈጽም መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ የፓልም የምግብ ዘይት ግዥን በገበያ ጥናት መሠረት እየፈጸመ አለመሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ አብዛኛውን የአገሪቱን አካባቢ እና ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ያመጣቸውን ዕቃዎች በወቅቱ ከወደብ ስለማያነሳ/ዕቃዉን ጭነው ሳያራግፉ በግቢ ውስጥ በመቆየታቸው  አላስፈላጊ የሆኑ የመጋዘን እና የዲሜሬጅ ክፍያዎች የተከፈሉ መሆኑ፣

- በኮርፖሬሽኑ ሳይወገዱ የቆዩ የተጎዱና የተበላሹ ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎች መኖራቸው፣
- ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና (minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን ፍላጎትና የገበያውን ሁኔታ መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት የማያካሂድ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ ለዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ ERP (Enterprise Resource Planning) የአሰራር ስርዓት በመገምገም ለችግሮቹ አፋጣኝ ማሻሻያ ያላደረገ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ሀሳብ/ አስተያየት መቀበል ብቻ ሳይሆን ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ፣ ቢሮ እና የመፍትሄ አሰጣጥ ሁኔታ የሚገልጽ የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ከመቀላቀሉ በፊት የነበረው ሂሳብ ተዘግቶ ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሒሳብ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይገባል፣
- የቀድሞው አለ በጅምላ ሲቋቋም ከባንክ የተበደረው ብድር በታህሳስ 2008 ዓ.ም. ወደ ኮርፖሬሽኑ ሲቀላቀል የብድሩ ዋናው (principal) ክፍያ እፎይታ ጊዜው በሦስት (3) ዓመት በመጠናቀቁ እ.ኤ.አ ከመስከረም 2016 ጀምሮ ዕዳና ወለድ በየሶስት (3) ወሩ ብር ወደ 21 ሚሊዮን (በዓመት 84 ሚሊዮን) ኮርፖሬሽኑ እየከፈለ በመሆኑና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥና ሽያጭ ለማከናወን በየቀኑ በተመሳሳይ ወለድ ምጣኔ የሚታሰብበት ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመሆኑ ይህ ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እንቅፋት በመሆኑ በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

በመሆን እና የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ችግሩ የሚቀረፍበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

- በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ግዥዎች ግልጽነትና ፍትሃዊነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለበት በስተቀር የፍጆታ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም ይኖርበታል፣ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት የነበረ ልምድ ተብሎ በኮርፖሬሽኑ እየተከናወነ ያለው የፓልም የምግብ ዘይት ግዥ የሚከናወንበት መንገድ በጥናት ተከልሶ ሂደቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ዋጋን ብቻ ሳይሆን ጥራትን (የህብረተሰብ ጤናንና ደህንነትን ከግምት ያስገባ) ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የዕቃ ግዢዎች የአገልግሎት መቆያ ጊዜ ቢያንስ ምን ያህል መሆን እንዳለበት በግልጽ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ የሚበላሹ ፣ጊዜ የሚያልፋቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ሊቀንስ/እንዳይኖሩ የሚያደርግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተለያየ ምክንያት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የደረሰና ያለፈ ለገበያ ሊቀርቡ የማይችሉ እቃዎችን በኮርፖሬሽኑ በተቀመጠው አሰራር መሠረት ሊያስወግድ ይገባል፣፡
- ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና (minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣
- ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን እና የገበያውን ሁኔታ ለመረዳትና ተፈላጊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፣ የሚከናወነው ጥናትም ለስትራቴጂክ ዕቅድ እንደግብዓት ሊያገለግል ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት አላማን ለማሳካትና በሁሉም አካባቢዎች ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት በመዘርጋትና ከዚህ በፊት በጥናት የተለዩትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ማቆያ መጋዘኖች እና መሸጫ መደብሮች ሊያስፋፋ ይገባል፣

- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ዓላማን ለማሳካት እንዲረዳው የተፈቀዱ የሥራ መደቦችን በተፈላጊው የሰው ኃይል ሊያሟላ እና ለሁሉም ሰራተኞች /ለባለሙያዎች/ የስራ መዘርዝር (Job Description) ተዘጋጅቶ እንዲሰጥና ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣
- ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ ERP (Enterprise Resource Planning) የአሰራር ስርዓት በመገምገም ችግሮችን በመቅረፍ ቴክኖሎጂውን በሙሉ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡

የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

## የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን እና አመሰራረት

1. የንግድ ዘርፉ በሀገር ውስጥ እና በውጪ ብቁና ተወዳዳሪ ሊያደርገው የሚችል አደረጃጀት እንዲኖረው ማድረጉ አስፈላጊ ስለሆነ በመንግሥት የልማት ድርጅትነት ሲንቀሳቀሱ የነበሩት አራቱ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አክስዮን፣ የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት፣ የግዥ አገልግሎት ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት /አለ በጅምላ/ ይሰጡ የነበረውን ምርትና አገልግሎት በተቀናጀ መልኩ ለህብረተሰቡ ለማሰራጨት እና ተጨማሪ ተልዕኮ ለመወጣት እንዲቻል በታህሳስ 12 /2008 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 369/2008 የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የተቋቋመ ሲሆን በተቋቋመበት ደንብ መሰረት የአራቱም ድርጅት መብትና ግዴታዎች ለኮርፖሬሽኑ እንዲሸጋገር ተደርጓል፡፡
ኮርፖሬሽኑ የሚተዳደረው በመንግስት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ሆኖ ተጠሪነቱም ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ራዕይ እና ተልዕኮ

### ራዕይ

2. በሀገር ውስጥ እና በዓለም ዓቀፍ ንግድ ሥርዓት ውስጥ በ2017 መጨረሻ በኢትዮጵያ ተመራጭ የንግድ ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

### ተልዕኮ

3. ዘመናዊ የግብይት ስርዓትንና የንግድ ውለታን አክብሮ በመስራት ጥራት ያላቸውን የተመረጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችን፣ መሰረታዊ ሸቀጦችን፣ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር በተወዳዳሪ ዋጋ በመግዛት፣ ለአርሶ አደሩና አምራቹ የገበያ እድል በመፍጠር ክምችት ይዞ ለሸማቹ ሕብረተሰብ በማሰራጨት እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የውክልና ግዥ በማካሄድና በግዥ ዙሪያ የማማከርና

የስልጠና አገልግሎት በመስጠት የሀገር ውስጥ ገበያን ማረጋጋትና የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲፋጠን አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ስልጣንና ተግባር

4. ደንብ ቁጥር 369/2008 እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ፤

- የተመረጡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶችንና፣ መሠረታዊ ሸቀጦችን ከአገር ውስጥ እና ከውጪ አገር በተወዳዳሪ ዋጋ ገዝቶ በማሰራጨት የአገር ውስጥ ገበያን ማረጋጋት ፤
- ሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ በተመረጠ አኳኋን ማስመረት፣ መግዛትና ማሰራጨት፣ ክምችት መያዝ፣ ለሀገር ውስጥ እና ለውጪ ገበያ ማቅረብ፤
- በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ ተመስርቶ የአገር ውስጥና የውጪ አገር ግዢዎችን መፈጸም መሸጥ፤
- የአርሶ አደሩ የማምረት ፍላጎት እንዲያድግ ለግብርና ምርቶች አስተማማኝ ገበያ እንዲፈጠር እገዛ ማድረግ፤
- ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት የግብይት አሰራር መዘርጋትና መፈፀም፤
- ለሥራው የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው አይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የምርምር፣ የትምህርትና የስልጠና ተቋማት መተባበር
- የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ግዥዎችን በሚመለከት የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የውክልና ግዢ መፈጸምና ስልጠና መስጠት
- የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቦንድ የመሸጥ፣ የመግዛት፣ በዋስትና የማስያዝ፣ ከአገር ውስጥና ከውጪ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ
- ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን በሚሰጠው አቅጣጫ ላይ በመመስረት በአገር ውስጥና በውጪ ሀገር ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ ስራ አመራር ግብዓቶችን ለማግኘት የሚያስችለው ኢንቨስትመንት መሳብም ሆነ

በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ ጥናት በማካሄድ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፤

### የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ዘርፍ/አለ በጅምላ/ ተግባርና ኃላፊነት፡-

- ህብረተሰቡ ለፍጆታ የሚጠቀምባቸው የተለያዩ መሠረታዊ ምርቶች ከሀገር ውስጥና ከውጪ አገር ግዥ መፈጸም፣
- ህብረተሰቡ ለፍጆታ የሚጠቀምባቸውን መሠረታዊ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ፣
- በፍጆታ ዕቃዎች የግብይት ሂደት የገበያ ማረጋጋት ሥራ መስራት፣
- ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የፍጆታ ዕቃዎች የግብይት አሠራር በመዘርጋት መፈጸም፣
- የፍጆታ ሸቀጦችን በተመረጠ አኳኃን ማስመረት፣ መግዛትና ማሰራጨት፣ ክምችት መያዝ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፣
- የተመረጡ የፍጆታ ዕቃዎችን ከሀገር ውስጥ ከውጭ አገር በተወዳዳሪ ዋጋ በመግዛትና በማሰራጨት የአገር ውስጥ የፍጆታ ሸቀጦችን ገበያ ማረጋጋት፣

## ፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ /የዘርፉ/ መዋቅር

5. የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ መንግስት የሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት አሁን በስራ ላይ ያለው አደረጃጀት በስድስት ድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬቶች እና በአምስት ዓላማ አስፈጻሚ መምሪያ ስራ አስኪያጆች የተደራጀ ሲሆን በአዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት እና በክልል ከተሞች በሚገኙ አራት በአጠቃላይ በሰባት የሽያጭ መደብሮች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ አባሪ 3 ተያይዟል

### የሰው ኃይል

6. የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ በ2009 ዓ.ም በፀደቀው ድርጅታዊ መዋቅር የሰው ሀይል ከኮርፖሬሽኑ አጠቃላይ 2713 ዕቅድ የዘርፉ 454 (ለአንድ ቅርንጫፍ የተፈቀደው 48) ሲሆን በታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም ወንድ 179 እና ሴት 95 ሰራተኞች በድምሩ 277 ሰራተኞች በስራ ላይ ይገኛሉ የነዚህ ሰራተኞች በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ማስተርስ 14 ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ 121 ፣ ዲፕሎማ 96 ፣ ከ 12ኛ ክፍል በታች 43 ናቸው ፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

7. ኮርፖሬሽኑ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከ2008 እስከ ጥር 2011 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ ለመግለጽ የበጀት ማስረጃ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ ማካተት አልተቻለም፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

8. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም በተመለከተ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

9. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ነው፡፡ የኦዲት ስራው የሸፈነው በዋናነት ከ2008 እስከ 2011 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

10. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ/ አለ በጅምላ/ ሲሆን በናሙና ተመርጠው በታዩት በሦስት ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር፣ በዋና መስሪያ ቤት መጋዘንና መሸጫ መደብር፣ በስምንት ሸማች የህብረት ስራ ማህበራት፣ ሁለት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እና በአንድ ንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ጠይቆ በመከለስ ነው፡፡ በናሙና የታዩት ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

11. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) "የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

12. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሦስት(3) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ሁለት (2) ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፥

I. ኮርፖሬሽኑ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የፍጆታ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር በመግዛት የሀገር ውስጥ ገበያን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፡፡

II. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን በዘመናዊ ሽያጭ ማዕከሎቹ በማከማቸት ከግሉ የንግድ ዘርፍ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ በቀጥታና በቸርቻሪዎች አማካኝነት ለተጠቃሚ በማድረስ በሀገሪቱ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈ አሰራርና ውድድር ላይ የተመሠረተ የግብይት ስርዓት በማጠናከር የሀገር ውስጥ ገበያን ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፣

- ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈና ውጤታማ የገበያ ማረጋጋት ሥራ ለመስራት የሚያስችለውን የፍጆታ ዕቃዎችን በዘመናዊ ሽያጭ ማዕከሎቹ የህብረተሰቡን/የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ክምችት የያዘ መሆኑን መገምገም፡፡
- ኮርፖሬሽኑ ከግሉ የንግድ ዘርፍ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ በቀጥታና በቸርቻሪዎች አማካኝነት የፍጆታ ዕቃዎችን ለተጠቃሚ በማድረስ በሀገሪቱ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈ፣ አሰራርና ውድድር ላይ የተመሠረተ የግብይት ስርዓት በማጠናከር የሀገር ውስጥ ገበያን ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፡፡

III. ኮርፖሬሽኑ በውስጡ ካሉ ሌሎች ዘርፎች፣ ከግሉ የንግድ ዘርፍ፣ ከማህበራት/ ከተጠቃሚው እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፤ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሠጠ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

13. ከላይ የተመረጡትን ሦስት(3) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ሁለት (2) ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub Audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 38 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተዘጋጁትም መመዘኛ መስፈርቶች ለኮርፖሬሽኑ ተልከው አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ አስተዳደርን (Financial Managmnet) በተመለከተ፣

14. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የስርጭት እና ግብይት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

15. ኮርፖሬሽኑ ከመመስረቱ በፊት የቀድሞው የኢትዮጵያ ንግድ ስራ ድርጅት / አለ በጅምላ/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 285/2005 ሲቋቋም፣

    - በብር 1 ቢሊዮን በተፈቀደ ካፒታል ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በተላለፈለት 256.9 ሚሊዮን (በጥሬ ገንዘብና በአይነት በተከፈለ ካፒታል እና
    - ኢንቨስትመንትን ፋይናንስ ለማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቀደም ሲል በ9.5 (በአሁኑ 10.5) ከመቶ ወለድ ምጣኔ በተገኘው ብድር ብር 596 ሚሊዮን ለ15 ዓመት ውል በመፈረም ለተገበ ግዴታዎች
        - ብር 256.4 ሚሊዮን ለውጭ ኮንሰልታንት፣
        - 102.6 ሚሊዮን እዛው ሳለ ለብድሩ ወለድ መክፈያና
        - 9 ሚሊዮን ለሠራተኞች ደመወዝ የዋለ መሆኑ እና

- በታህሳስ 2008 ዓ.ም ድርጅቱ ወደ ኮርፖሬሽኑ ሲቀላቀል የብድሩ ዋናው (principal) ክፍያ እፎይታ ጊዜው በሦስት(3) ዓመት በመጠናቀቁ እ.ኤ.አ ከመስከረም 2016 ጀምሮ ዕዳና ወለድ በየሶስት (3) ወሩ ብር ወደ 21 ሚሊዮን (በዓመት 84 ሚሊዮን) ኮርፖሬሽኑ እየከፈለ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ (ከፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ/አለ በጅምላ ከመጣ ብድር / በየቀኑ በተመሳሳይ ወለድ ምጣኔ የሚታሰብበት ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመስራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- የቀድሞው የኢትዮጵያ ንግድ ስራ ድርጅት (አለ በጅምላ) ወደ ኮርፖሬሽኑ ከመቀላቀሉ በፊት ሂሳቡ ተዘግቶ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፣

- የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የ2008፣ 2009 እና 2010 በጀት ዓመት የተዘጋ የሒሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣

16. በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ በዕቅድ ደረጃ ምን ያህል ደንበኞች እንደተያዙ እና አሁን ላይ ያሉ ደንበኞች እና ደንበኝነታቸውን ያቋረጡትን እንዲሁም ተጨማሪ ደንበኞችን ለመሳብ የተቀመጠ ዕቅድን የሚገልጽ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፣

17. የዘርፉ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከባንክ ከተገኘ 596 ሚሊየን ብር ውስጥ 224,680,220 ሚሊየን ለግንባታ እና ቋሚ ዕቃ ግዥ ሲሆን 256 ሚሊየን ብር ደግሞ በአማካሪነት አለ በጅምላን ላቋቋመው AT-Kearney ለተባለ ድርጅት መከፈሉ፤ በመሆኑም 480 ሚሊየን ብር ለአማካሪ፣ ለግንባታ እና ለተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች የተከፈለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

18. ኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ

  - በአጠቃላይ የቀድሞው አለ በጅምላ ለመነገጃ ገንዘብ ይዞ ስራ የጀመረው
    - በካሽ የተከፈለውን 154 ሚሊየን ብር እና
    - ከባንክ ብድር 596 ሚሊየን ብር ውስጥ ለአማካሪ፣ ለቋሚ እቃ እና ግንባታ ተከፍሎ የተረፈውን 116 ሚሊየን ብር

በድምሩ 270 ሚሊየን ብር በመነገጃ ካፒታልነት ይዞ ስራ እየሰራ የሚገኝ ዘርፍ መሆኑን፣

- በዚህ ምክንያት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30/2011 ድረስ ለባንክ ዕዳ ብር 67,298,982.32፣ ብር 200,091,736.67 ወለድ በድምሩ 267,390,718.99 ሚሊየን ብር መከፈሉ፤
- ኮርፖሬሽኑ የመዋለ ነዋይ ችግር እንዲቀረፍለት በተለያየ ጊዜ ለንግድ ሚኒስቴር እና ንግድ ሚኒስቴር ደግሞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑ፤
- አለ በጅምላ ስራ በጀመረበት ጊዜ ተግባራዊ ያደረገው Micro soft Dynamic Nov Enterprise Resource Planning (ERP) የተወሰነውን ስራ ማለትም ግዥ፣ ስርጭት በERP እየሰራ የተወሰነውን ደግሞ ግዥ እና ስርጭት በሰነድ ብቻ በመስራቱ ምክንያት በERP ወይንም በሰነድ ሂሳብ መዝጋት የቻለው የ2008

በጀት አመት ሲሆን የ2009 እና 2010 በጀት አመት ሂሳብ ለመዝጋት ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራውን እየሰራ መሆኑን፤

- የ2011 ሂሳብን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ በERP እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

19. ይሁን እንጂ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የዘርፉ ሒሳብ ባልተዘጋበት ሁኔታ ኮርፖሬሽኑ ኪሳራ ውስጥ መሆኑን በ2008፣ 2009 እና 2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በመገለጹ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

20. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የስርጭት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በማከናወን አሰራሩን ሊያሻሽል፤ የዘርፉን አቅራቢና ተጠቃሚ ደንበኞችን በተጠናከረ ሁኔታ መሳብ ካልቻለ እና የተገባው ግዴታ እንዲሸፈንለት ካላደረገ እንደ ሀገር የፍጆታ ዕቃዎች የተጠናከረ የገበያ ማረጋጋት ስራ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡

### የፍጆታ ዕቃዎች የግዥ ዘዴን በተመለከተ፣

21. ኮርፖሬሽኑ የሚፈጽማቸውን የፍጆታ ዕቃ ግዥዎች በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን እና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የግዥ ዕቅድ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡

22. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ከተገዛው ግዥ ውስጥ መሠረታዊ ሸቀጦች /ዘይትና ስኳር/ (በ2008 በጀት ዓመት 52%፣ በ2009 82% እና 2010 84%) መሆኑና ቀሪው (በ2008 በጀት ዓመት 48%፤ በ2009 18% እና በ2010 16%) የፍጆታ ዕቃዎች መሆናቸው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. በኮርፖሬሽኑ ከውጭ የሚገቡ የፓልም የምግብ ዘይቶች ከኢንዶኔዥያ እና ማሌዥያ ብቻ ተገዝተው የሚገቡ መሆኑ፤ ሌሎች የተለያዩ ሀገራት አቅራቢዎች በጨረታ ተወዳድረው እንዲያቀርቡ ዕድሉን ያላመቻቸ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

24. የፓልም የምግብ ዘይት ግዥዎች ውል እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣ የኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የአገር ውስጥ የግዥ ውል ላልተወሰነ ጊዜ ጸንቶ የሚቆይ መሆኑ፣

25. ስለጉዳዩ የዘርፉ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የውጭ ግዥ በተመለከተ በዋጋ መጠየቂያ የሚገዛ ቢሆንም የሀገር ውስጥም ተመሣሣይ መሆኑ፤ በግልጽ ጨረታ ግዥ የማይፈጸምበት ምክንያት አንዳንዶቹ ምርቶች ለምሳሌ ፓልም ዘይት በሰአት

ወይንም በየቀኑ ዋጋው የሚቀያየር በመሆኑ፤ ሌሎች ሸቀጦችም በተመሳሳይ ሁኔታ በዋጋ መጠየቂያ የግዥ ዘዴ የሚገዙ እና በተፈቀደው የግዥ መመሪያ መሰረት ግዥው በዕቅድ እና በኮሚቴ እየተመራ የሚገኝ መሆኑ፡፡ ከዕቅድ ጋር ለማጣጣም የcapital ችግር እና LC አለመፈቀድ እና እንደ ዘርፍ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ በየቀኑ የመለዋወጥ ችግር የሚያጋጥም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

26. የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ

- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ መሰረታዊ ሸቀጦችን /ዘይትና ስኳርን/ ለመግዛት የሚያስፈልገው ገንዘብ እስከ 927 ሚሊየን ብር መድረሱ፤
- በተለይም የፓልም የምግብ ዘይት የ4 ወር ክምችት እየተያዘ መሰራት ያለበት በመሆኑ የእቃ ዋጋ፣ የባህርና የመሬት የትራንስፖርት፣ የመጫኛ እና ማውረጃ የጅቡቲ customs clearance ጨምሮ መንግስት በድጎማ የሚያስገባውን የምግብ ዘይት ዘርፉ እንዲያቀርብ ተጨማሪ ሀላፊነት ሲሰጠው የነበረውን የመነገጃ ገንዘብ ችግር ከግንዛቤ ያስገባ ባለመሆኑ በወቅቱ ያለውን የመነገጃ ገንዘብ የህብረተሰቡ አንገብጋቢ እና መሰረታዊ ወደ ሆነው የምግብ ዘይት የማዘዋወር ስራ መሰራቱ፤
- ይህም ሆኖ ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ማቅረብ የሚገባውን የምግብ ዘይት በመነገጃ ገንዘብ እጥረት እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተፈጠረው የውጭ ምንዛሬ ጉድለት ሙሉ በሙሉ ለማቅረብ እንዳልቻለ፣
- በዚህ ምክንያት ሌሎች ሸቀጦችን ማቅረብ ላይ የተፈጠረ ችግር መኖሩ፤
- ከሀገር ውስጥ ለሚገዙ ሸቀጦች ባለበት የመነገጃ እጥረት ከአቅራቢዎች ጋር በሚያደርገው የዱቤ ግዥ አንዳንድ አቅራቢዎች ለኮርፖሬሽኑ የማቅረብ ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን፣
- ዘርፉ ወደ ኮርፖሬሽን ከመዋሃዱ በፊት የእቃ ግዥ ስርዐቱ እና የዋጋ አወጣጡ ላይ መስተካከል የሚገባው ችግር እንደነበር ወደ ኮርፖሬሽኑ ከተቀላቀለ በኋላ ግዥ የሚከናወነው ኮርፖሬሽኑ ባዘጋጀው አዲስ የሸቀጥና የንብረት ግዥ መመሪያ መሆኑን፣

- በአብዛኛው የፓልም ምግብ ዘይት የሚመረተው እና ጥሬ እቃው የሚገኘው የኦዲት ቡድኑ ከጠቀሳቸው ሀገሮች ሲሆን ከዚህ ውጭ አንድም ድፍድፋን በማስመጣት አልያም ከአምራቹ ለመግዛት (Traders) የሚያቀርቡበት ስርዓት ነው ያለው፡፡ በመሆኑም ከአምራቹ ከመግዛት እና ከTraders ከመግዛት የትኛው ይሻላል የሚለውን የዋጋ አማራጭ ለማጥናት ቀደም ብሎ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር፣ ከየንግድ ሚኒስቴር እንዲሁም ቀድሞ የፓልም ዘይት ያስመጣ ከነበረው መንግስታዊ የልማት ድርጅት /ጅንአድ/ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተወጣጣ ቡድን ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ በማጥናት እነዚህ የተጠቀሱት ሀገሮች አምራችና አከፋፋይ መሆናቸው ሀገሪቱን በዋጋ ተጠቃሚ ሊያደርግ እንደሚችል በመረጋገጡ በነዚህ ሀገሮች የሚገኙትን አምራቾችና አከፋፋዮች በማወዳደር ግዥ እየተፈጸመ እንደሚገኝ፤

ገልጸዋል፡፡

27. በረቂቅ ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ የፓልም የምግብ ዘይት ዋጋን የሚያወጣው ንግድ ሚኒስቴር መሆኑን፣ በተሰጣቸው ዋጋ መሸጥ ግዴታ መሆኑን፣ ነገር ግን የተሻለ ዋጋ ለማግኘት የተለያዩ የፓልም የምግብ ዘይት አቅራቢዎችን በኢ-ሜል በማወዳደር ግዥ የሚፈጸም መሆኑ፡፡

28. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃ ግዥ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን ሲገባ ሁለትና ከዚያ በላይ አምራች/ አቅራቢዎች መኖራቸውን ካረጋገጠ በኋላ የመጀመሪያው አማራጭ በግልጽ ጨረታ መግዛት መሆኑ እየታወቀ በግልጽ ጨረታ ግዥ መፈጸሙን የሚገልጽ ማስረጃ፣ በቡድኑ የተጠና የፓልም የምግብ ዘይት የዋጋ አማራጭ ጥናት ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበለት በመሆኑ ከላይ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

29. ኮርፖሬሽኑ የሚፈጽማቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ አስቀድሞ በግዥ ዕቅድ የማይመራ፣ አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልፅ ጨረታ የማይገዛ እና የህብረተሰቡን ወቅታዊ የግዥ ፍላጎት የማያጠና እንዲሁም የወቅቱን የመንግስት የግዥ ስርዓት በማጥናት መመሪያውን የማያሻሽል ከሆነ የኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ ይሆናል ብሎ ለመግለጽ ያዳግታል፡፡

## ጥራትን መሠረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ማከናወኑን በተመለከተ

30. ኮርፖሬሽኑ ለሚገዛቸው የፍጆታ ዕቃዎች ምርት ትክክለኛ የሆነ የጥራት ደረጃ (Standard) እንዲወጣላቸው፣ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት (Specification) እንዲዘጋጅ እና በመረከቢያ ሠነድ ተሞልቶ ገቢ ከመደረጉ በፊት ዕቃው/ሸቀጡ የተጠየቀውን መስፈርት ማሟላቱን በሚመለከተው ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. ኮርፖሬሽኑ

- በፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ወጪን (ዋጋን) እንጂ ጥራትን ትኩረት የማይሰጥ መሆኑ፡- በአብዛኛው ዘርፉ የሚያስመጣው የፓልም የምግብ ዘይት የጥራት ደረጃው CP10 (የሚረጋውን) ሲሆን፣ ጥራት ያላቸው ግን CP8 መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጦ በታየ የባህርዳር ቅርንጫፍ መደብር ከፊንጫ ተገዝቶ የሚመጣ ስኳር መያዣው ከረጢት ጥራት የሌለው በቀላሉ የሚቀደድ በመሆኑ ስኳሩ እንዲባክን፣ ሌላ ከረጢት እየተገዛ ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑን ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ እና በአካል ተገኝቶ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



*ምስል 1. እንደገና በተጨማሪ ወጪ በከረጢት በማሸግ ለገቢያ የሚቀርቡ የስኳር ምርቶች*

32. በኮርፖሬሽኑ በሚያዝያ 17 2008 ዓ.ም አላሚ (አረብ ማሌዥያ) ከተባለ የፓልም የምግብ ዘይት አቅራቢ ድርጅት የተገዙ

- ባለ 3 ሊትር 141 ጀሪካን
- ባለ 5 ሊትር 234 ጀሪካን እንዲሁም
- ባለ 20 ሊትር 1,568 ጀሪካን

ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ ለሽያጪ መቅረብ እንደማይችሉ የተረጋገጠ ቢሆንም በውል ስምምነቱ መሰረት ተከታትሎ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. በተጨማሪም አቅራቢው ድርጅት በዋጋ ማቅረቢያው መሰረት በእያንዳንዱ ኮንቴይነር ውስጥ መጫን የነበረበት የፓልም የምግብ ዘይት መጠን ባለመጫኑ ምክንያት ጉድለቱን ለማካካስ ተጨማሪ ኮንቴይነሮችን አቅራቢው የላከ በመሆኑ ኮንቴይነሮችን በባህርና በየብስ ለማጓጓዝ

- በሌተር ኦፍ ክሬዲት ቁጥር TF1612418371 እና TF1612403593 ለተገዙት ለባለ 3 ሊትር የፓልም የምግብ ዘይት ተጨማሪ 20 ኮንቴይነሮች በመላኩ ብር 1,078,901.82፣
- እንዲሁም በሌተር ኦፍ ክሬዲት ቁጥር TF1612469409 ለተገዛ ለባለ 5 ሊትር ዘይት ተጨማሪ 7 ኮንቴይነር በመላኩ ብር 411,528.26 ፣

**በድምሩ ብር 1,490,430.08** ኮርፖሬሽኑ አለአግባብ እንዲያወጣ መደረጉን በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. የኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ዘርፍ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተገዝተው የሚገቡ የፍጆታ ዕቃዎች የጥራት ደረጃ ያላቸው መሆኑን የ Quality supervisor ዕቃዎች ገቢ በሚሆኑበት ግዜ እየፈተሸ የሚያስገባ መሆኑ፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ተቆጣጣሪ እና የጤና እና የምግብ ምርቶችን ደህንነት ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት እንደ ሶስተኛ ወገን ምርቶችን ፈትሾ እንድንሸጥ ወይንም ወደ ሀገር ዉስጥ እንድናስገባ በሚፈቅድበት ጊዜ ሽያጭ የሚፈጸም መሆኑን እና በመንግስት የሚረጋ CP10 የፓልም የምግብ ዘይት እያስመጣን እንዲሸጥ የተፈቀደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

35. የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ዘርፉ የእቃዎችን ጥራት በተመለከተ በልዩ ትኩረት እየሰራ መሆኑ፣ በተለይም ከውጭ የሚያስገባው የምግብ ዘይት የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን (FMHACA) ባወጣው

መስፈርት ተመርምሮ የሚገባ መሆኑ፤ በሀገር ውስጥ የፓልም የምግብ ዘይት የሚያስመጡት አስር አስመጪዎች CP10 የፓልም ምግብ ዘይት መሆኑ ዘርፉ ለሸቀጦች ጥራት ትኩረት መስጠት እንዲችል በአደረጃጀቱ የጥራት ቁጥጥር ክፍል በመምሪያ ደረጃ እንዲዋቀር እና በቂ የጥራት መቆጣጠሪያ መመሪያዎች እንዲኖሩት መደረጉ፣

36. የስኳር መያዣ ከረጢቱን በተመለከተ ስኳር ኮርፖሬሽን ጋር ያለ ችግር መሆኑ፤ ለችግሩ የተደረገ ማስተካከያ አለመኖሩ ከዚህ አኳያ ብክነቱን ለመከላከል ከሱቅ እየተገዛ የመተካት ስራ የሚሰራ መሆኑን እና በተለይም ትራንስፖርተሩ ሲጭን በሚያደርሰው ጉዳት ከረጢቱን እንዲተካ የማድረግ ስራ እየተሰራ መሆኑን መግለጻቸው፤

37. የተጠቀሰው አቅራቢ 27 ኮንቴነር የሚሆን ጉድለት ያስከተለ አቅርቦት በማድረጉ እንዲተካ መደረጉን፡፡ነገር ግን በሁለተኛ ዙር የጎደለውን በሚተካበት ጊዜ የተከፈለ የትራንስፖርት ክፍያ በአቅራቢው መሸፈን ሲገባው በኮርፖሬሽኑ የተሸፈነ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት አለአግባብ የተከፈለውን ብር ለማስመለስ ጥረት እየተደረገ ሲሆን አቅራቢው ዘይት ግዥ በምታወጡበት ጊዜ በአሸናፊው ዋጋ የተወሰነ ኮንቴነር እንዳቀርብ እድሉን ስጡኝ ክፍያ ስትፈጽሙ ቀንሳችሁ ክፈሉኝ ወይም መመለስ የሚገባኝን ያህል ብር ከዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢው ቀንሼ ልሸጥላችሁ የሚል ሀሳብ በማቅረቡ ከመንግስት የግዥ አሰራር እና የድርጅቱን ብር ከማስመለስ አኳያ አግባብነቱ ላይ እየተወያዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

38. ይሁን እንጂ የሚረጋው CP10 የፓልም የምግብ ዘይት ተገዝቶ እንዲገባ የትኛው የመንግስት አካል ውሳኔ እንዳስተላለፈ እና ከዚያም በኃላ በጥናት ተከልሶ ግዥ እየተፈጸመ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣ የጎደለውን የፓልም የምግብ ዘይት ማስመለሱን እና የስኳር መያዣ ከረጢት የጥራት ችግር ለመቅረፍ ያስቀመጠውን የመፍትሄ አቅጣጫ የሚገልጽ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ባለመቅረቡ አስተያየቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

39. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ምርት በመስፈርት (Specification) መሰረት ትክክለኛ የሆነ የጥራት ደረጃ (Standard) መኖሩን አረጋግጦ የማይገዛ ከሆነ ለዕቃዎች ጉድለት፣ የጥራት ችግር እና ለተጨማሪ ወጪ፤ እንደ ሀገር ደግሞ ወደ ገበያ ያለማረጋጋት እና ለከፍተኛ የሀብት ብክነት ይዳርጋል፡፡

## ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ማድረግን በተመለከተ

40. ኮርፖሬሽኑ የተቀላጠፈና በዘመናዊ የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ (በተለይ መሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችን) ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

41. ኮርፖሬሽኑ በዘርፉ የተቀላጠፈ እና በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ እየሰራ አለመሆኑንና ያሉት ማከፋፈያዎቹም በአዲስ አበባና በተወሰኑ ከተሞች ብቻ የተወሰነ መሆኑ ታውቋል፡፡

42. በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በኦዲት ወቅት የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አለ በጅምላ ገበያ ለማረጋጋት ችግር የሆነበት ሁሉንም አይነት /Brand የፍጆታ ዕቃዎች ማቅረብ አለመቻሉን፤ የውጭ ሽያጭ ሰራተኞች/ Direct sellers ከውጭ በሚሰበሰቡት መረጃ እና ደንበኞች በሚሠጡት መረጃ መሰረት የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ አቅርቦት መኖሩን፤ ነገር ግን አንዳንድ ዕቃዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተፈላጊ መሆናቸውን በጥናት ካረጋገጡ በኋላ ማስገባት/ማቅረብ የማይችሉበት የሀገር ዉስጥም ሆነ የዉጭ ሀገር ምርቶች መኖራቸው፤ ምክንያቱ ደግሞ አምራቾች ብቸኛ ወኪል ስለሚኖራቸው እና አለ በጅምላ ግዥ የሚፈፅመው በዱቤ በመሆኑ፤ ነገር ግን በዱቤ ምክንያት የተፈጠረዉን ችግር እንደምርቱ ተፈላጊነት እና አዋጭነት በማየት በካሽ ለመግዛት ጥረት እየተደረገ መሆኑ፤ የምርቶች ፍላጎት ወቅትን መሠረት ያደረገ እና አቅርቦት በፍላጎት ጥናት ላይ ተመስርቶ የሚሰራ መሆኑን ፤ አሁን ባለው 7 መደብር ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ አድርጓል ማለት የማይቻል እንዲሁም እንደ ሀገር ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ያለመደረጉ ለቀጣይ በሌሎች አካባቢ አዳዲስ የመሸጫ መደብሮችን ለመክፈት እቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

43. ይሁን እንጂ የውጭ ሽያጭ ሰራተኞች/ Direct sellers ከውጭ የሚሰበስቡት መረጃ የገበያ ዋጋ መረጃ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

44. ኮርፖሬሽኑ የተቀላጠፈና በዘመናዊ የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ የማያደርግ ከሆነ እንደ ሀገር የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት ገበያ የማረጋጋት ድርሻ ለመወጣት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**ዕቃዎች ደረጃውን በጠበቀ መጋዘን ውስጥ እንዲከማቹ ማድረግን በተመለከተ**

45. ኮርፖሬሽኑ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ገዝቶ የሚያስመጣቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ደረጃውን ጠብቆ በተገነባ መጋዘን ውስጥ እንዲከማች ሊያደርግ ይገባል፡፡

46. የቀድሞው የኢትዮጵያ ንግድ ድርጅት ሲመሰረት ድርጅቱ እንዲቋቋም ባጠኑት አማካሪዎች (A.T Kearney) ጥናት መሰረት በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ በሦስት (3) ዓመት በ 27 ከተሞች 36 መደብሮች ይከፈታሉ ተብሎ ቢጠበቅም በአምስት(5) ከተሞች 7 መደብሮች ብቻ መከፈታቸው (በአዲስ አበባ 3፣ ባህርዳር 1፣ ደሴ 1፣ ሻሸመኔ 1 እና ሀዋሳ 1 )፤ ይህም ይከፈታሉ ተብለው ከተጠበቁት 36 መደብሮች ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ 19.44 በመቶ ብቻ በመሆኑ የማከማቻ መጋዘኖችና የመሸጫ መደብሮች ያልተስፋፉ መሆኑ፤

47. ኮርፖሬሽኑ የዘይት ማስቀመጫ ለእህል እና ቡና ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን መጋዘን ለማከማቻ መጠቀም እየቻለ ደረጃውን የጠበቀ አይደለም አንጠቀምበትም በሚል ምክንያት እና ተለዋጭ መጋዘንም ቢሆን በኪራይ ባለመዘጋጀቱ፤ በኮሜትና በሞጆ ደረቅ ወደብ ውስጥ በወቅቱ ሳይራገፉ ከሶስት ወራት በላይ ላስቆጠሩ ኮንቴይነሮች ከብር 7 መቶ ሺ በላይ ለመጋዘን ኪራይ የተከፈለ ሲሆን ኮንቴይነሮቹም በተገቢው ቀን ባለመነሳታቸው /ዕቃዉን ጭነው ሳያራግፉ በግቢ ውስጥ በመቆየታቸው ከሐምሌ 2016 እስከ ጥቅምት 2016 ድረስ ብቻ ብር 1,654,215.00 ሚሊዮን ዲመሬጅ ያለአግባብ መከፈሉን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ መደብሮች፣

- በባህርዳር እና ሀዋሳ በሽያጭ መደብሩ የግቢ ዙሪያ ወለሉ ውሃ የሚያቁር መሆኑ፤
- የክፍሎቹን የአየር ዝውውር ለመቆጣጠር የሚያስችል የአየር ሁኔታ ማስተካከያ /ventilator/ የሌለው መሆኑ፣
- በቃሊቲ እና በባህርዳር በቅርንጫፍ ሽያጭ መደብሩ ለሚነሳ ድንገተኛ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ወደ ኮርፖሬሽን ከተዋሃደ ጀምሮ ያልተሞላ ወይም ማሻሻያ ያልተደረገለት መሆኑ፤

- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ (Firist Aid Kit) ጊዜው ያለፈበት መሆኑ፣
- በቃሊቲ መጋዘን እና መሸጫ መደብር፣ በሀዋሳ መሸጫ መደብር የመጋዘኑ ወለል የተቆፋፈረ/የተጋጋጠ መሆኑ፣



*ስዕል 2 . በሀዋሳ የመሸጫ መደብርና ማከማቻ/ማቆያ በአንድላይ*

- በሀዋሳ ሽያጭ መደብር ክምችትና ሽያጭ በአንድ መጋዘን /መሸጫ መደብር መሆኑ ለአሰራር ስርአቱ ወይም ክምችት እና ሽያጭ ስራ እንዳይቀላጠፍ ማድረጉ፣

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከዘርፉ በኦዲት ወቅት እና ከኮርፖሬሽኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠ አስተያየት ፣

49. አለ በጅምላ በሀገር ደረጃ ሲቋቋም 20 ከመቶ የገበያ ማረጋጋት ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ የነበረ ሲሆን፤ በተጠናው ጥናት መሠረት በ 27 ከተሞች 36 መደብሮች ይከፈታሉ ተብሎ ቢጠበቅም በአምስት ከተሞች 7 መደብር ብቻ መከፈታቸው እውነት ነው ይህንን ዕቅድ ለመተግበር ኮርፖሬሽኑ በአሁኑ ወቅት የተጠናውን ጥናት በድጋሚ ማየትና አዋጭነቱንም ማረጋጋጥ ስላለበት በረጅም ጊዜ ዕቅድ የተያዘለት መሆኑ፤

50. የሀዋሳን መጋዘን ጉዳይ በተመለከተ ችግሩን በመለየት አዲስ ማከማቻ መጋዘን በመስራት መፍትሄ ለመስጠት ለከተማው መስተዳድር የመሬት ጥያቄ ቀርቦ ፈጥኖ ምላሽ ማግኘት ባለመቻሉ ክትትል እየተደረገበት መሆኑን፣

51. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የመጋዘን /የመደብር ማስፋፋት ስራ ሳይሰራ በመገደቡ፤ በተመቻቸ ሁኔታ ክምችት ባለመያዙ ለብክነት እና የተጠናከረ የገበያ ማረጋጋት ስራ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡

## የተበላሹና ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎችን በተመለከተ

52. ኮርፖሬሽኑ የሚሰራጩ የፍጆታ ሸቀጦች የተበላሹ እና የጎደሉ ካሉ ተለይተው እና ተቆጥረው ወይም ተመዝነው ለየብቻ እንዲቀመጡ፣ በተበላሹ እና በጎደሉ የፍጆታ ሸቀጦች በውል መሰረት የሚተኩ ካሉ እንዲተኩ ሊያደርግ ይገባል፡፡


53. የመድን ሽፋን የተገባለት ብዛቱ 1,996 ካርቶን ዋጋው ብር 591,547.34 የሆነ ባለ 5 ሊትር የፓልም የምግብ ዘይት የጫነ ኮንቴይነር ልዩ ስሙ ዶቢ በተባለ ቦታ ሴፕቴምበር 10/2015 አደጋ ደርሶበት በጊዜው ብር 15,000.00 አረቦን ባለመከፈሉ የኢንሹራንስ ካሳ ያላገኘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

54. በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ በአዲስ አበባ ባሉት የመሸጫ መጋዘኖች የተጎዱ ወይም የተበላሹ እንዲሁም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎች (ምግብና ምግብ-ነክ፣ መድሃኒት-ነክ ያልሆኑ የመዋቢያ ዕቃዎች /ኮስሞቲክ እና የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች) ዋጋቸው ብር 607,862.98 እንዲወገዱ በተጻፈ ደብዳቤ በቀን 01/10/2010 ዓ.ም በቁጥር ፍ/ጥ/ን/ዘ 01/5/2/20 ተጠይቆ በቀን 14/12/2010 ዓ.ም በቁጥር 02/21/16/346 በኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋጋቸው የማይታወቅ አገልግሎት ላይ የማይውሉ የምግብ ዓይነቶችን በመለየት የተወገዱ መሆኑን ገልጿዋል፡፡

55. ይሁን እንጂ በቃሊቲ እና በሌሎች ቅርንጫፍ ማከማቻ መጋዘንና መሸጫ መደብሮች

- ከአንድ እስከ አራት ዓመት የተቀመጡ ጊዜ ያለፈባቸው እና ጉዳት የደረሰባቸው/ የተበላሹ የፍጆታ ዕቃዎች (ምግብና ምግብ-ነክ፣ መድሃኒት-ነክ ያልሆኑ የመዋቢያ ዕቃዎች /ኮስሞቲክ እና የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች) ለምሳሌ፡ በመርካቶ ከብር 60,000 በላይ የሚገመቱ ፣ በባህርዳር ፣ ሀዋሳ እና በቃሊቲ ዋጋቸው የማይታወቅ ዕቃዎች መኖራቸውን እና
- ለነዚህ የፍጆታ ዕቃዎች የተለየ ማስቀመጫ ክፍል ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን

የመጋዘን/ የመደብር ሀላፊዎች በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የገለጹ ሲሆን ሁኔታውንም በአካል ተገኝቶ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ስዕል 3. የተበላሹ የፍጆታ ዕቃዎች በቃሊቲ በመጋዘን ውስጥ



ስዕል 4. የተበላሹ ምርቶችና ጥቅም ላይ የሚውሉ የፍጆታ ዕቃዎች በቃሊቲ አንድ መጋዘን ውስጥ

56. ኮርፖሬሽኑ በዘርፉ በተከታታይ የሚከሰቱ የፍጆታ ዕቃዎች የመጠቀሚያ ጊዜ ማለፍ፣ የብልሽትና ብክነት ችግሮች  መቀነስ ያልቻለ መሆኑ፣ ከተከለሰ ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. በኦዲት ወቅት የዘርፉ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እንደዘርፍ የጥራትና የማስወገድ መመሪያ ባይኖርም እንደ ኮርፖሬሽን የሚጠቀሙት መመሪያ መኖሩን ፤የተበላሹ ምርቶችን ወይንም የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምርቶች

በየአመቱ የማስወገድ ሥራ የሚሰራ መሆኑ፣ ነገር ግን በ2011 በጀት ዓመት መስከረም ላይ የሀዋሳ ሽያጭ መደብር ምርቶችን ለማስወገድ ባደረገው ጥረት ላይ ከተማው ላይ በተፈጠረው አለመረጋጋት ምክንያት በሚወገድበት አካባቢ የሚኖሩ የከተማው ነዋሪዎች ፈቃደኛ ያለመሆን አዝማሚያ በመፈጠሩ እስከ አሁን ማስወገድ ያልተቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

58. የኮርፖሬሽኑ የስራ ሃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት ስለጉዳዩ በሰጡት ምላሽ አለ በጅምላ ሲቋቋም በገበያ ተፈላጊነታቸው እና የዋጋ ሁኔታቸው በአግባቡ ሳይጠና መደብሮቹን ፈጥኖ ለመክፈት ሲባል የተገዙና የተለያዩ የሽያጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ምርቶቹን ለመሸጥ ቢሞከርም የመጠቀሚያ ጊዚያቸው ስላለፈ መወገዳቸውን ገልጸዋል፡፡

59. ኃላፊዎቹ እቃዎች እየተወገዱ ነው ይበሉ እንጂ የኦዲት ቡድኑ በኦዲት ወቅት ከአንድ እስከ አራት ዓመት ሳይወገዱ የቆዩ የተጎዱና የተበላሹ ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎች መኖራቸውን በኦዲት ወቅት በአካል ምልከታ ለማረጋገጥ በመቻሉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

60. ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ካላከናወነ፣ የተጎዱና ጊዜ ያለፈባቸውን የማይተካና የማያስወግድ ከሆነ እንደ ተቋምም ሆነ እንደ ሀገር ከፍተኛ የሀብት ብክነት ያስከትላል፡፡

## የፍጆታ ዕቃዎች ክምችትን በተመለከተ

61. ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና(minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከውጭ አገር ተገዝተው ለሚገቡ ምርቶች ቢያንስ ለሶስት ወር የገበያ ፍላጎት የሚሆን ምርት ሊይዝ ይገባል ፡፡

62. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና(minimum stock level) ከፍተኛ(Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ተወስኖ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑን ታውቋል፡፡

63. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ በተሟላ መልኩ (ህብረተሰቡ የሚፈልገውን የፍጆታ ዕቃዎች በሚፈለገው ወቅት፣ መጠን/ኪታ እና በተመጣጣኝ

ዋጋ) ደንበኞች ተኮር አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ፣ ደንበኞች የለመዷቸውን አዲስ ምርቶች ከክምችት ሲያልቁ በፍጥነት የማይተካ መሆኑ (አነስተኛ የክምችት መጠን ወሰን የሌለው መሆኑ) በኦዲት ወቅት በናሙና የታዩ የዘርፉ ቅርንጫፍ መደብሮች፣ ሸማች ማህበራት እና የከተማና የክልል ንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ/ቢሮ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

64. በኦዲት ወቅት ስለጉዳዩ የዘርፉ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሙሉ በሙሉ ሁሉም ዕቃዎች ክምችት እንደማይያዙ፣ አንዳንድ ምርቶች ደግሞ ሸጠው ከጨረሱ በኋላ መልሰው ለመግዛት አምራቹ ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም በሚያጋጥመው የጥሬ እቃ አቅርቦት ምክንያት ከክምችት ውጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ቢኖርም በቂ በሆኑ ምርቶች ላይ ክምችት ተይዞ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

65. የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ በዘርፉ ዕቃዎች ክምችት ላይ ከማለቃቸው በፊት ትዕዛዝ በየሳምንቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ነገር ግን የሚሰበሰበውን ትእዛዝ ለአቅራቢዎች በሚሰጥ ጊዜ ሁሉም አቅራቢዎች በፍጥነት ያለማቅረብ በተለየ ደግሞ በካሽ ለሚገዛቸው ቅድሚያ የመስጠት ነገር እያጋጠመ መሆኑ፣ በቅርብ ጊዜ በተለይም በከፍተኛ ሁኔታ ሸማቹ ህብረተሰብ የሚፈልጋቸውን ምርቶች ዘርፉ በካሽ እንዲገዛ የሚል ሀሳብ ቀርቦ በዚሁ አግባብ እየተከናወነ መሆኑን፣ ትልቁ ችግር ግን አሁንም ያልተፈታው ነገር ቢኖር አምራች የሆነ አካል ሻጭ መሆን የለበትም የሚል የንግድ መመሪያው ቢከለክልም በቤተሰብ እና መሰል ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያቶች ለአንድ ሰው ብቻ የማከፋፈል እድሉን የመስጠት ሁኔታ ስለሚስተዋል ዘርፉ እጅግ ከፍተኛ ችግር እየገጠመው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

66. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ፣ ህብረተሰቡ የፍጆታ ዕቃዎች በሚፈልግበት ወቅት ማቅረብ ስለማያስችለው እንደ ሀገር የተጠናከረ ገበያ ማረጋጋት ስራ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡

### የገበያ ጥናት መካሄድን በተመለከተ

67. ኮርፖሬሽኑ በዋነኛነት የሚያገለግለውን የህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ በጥናቱም መሰረት እጥረት ያለባቸውን የመሰረታዊና የፍጆታ ሸቀጦችን በወቅቱ ወደ ገበያ በመግባት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን ሊያረጋጋ ይገባል፡፡

68. ኮርፖሬሽኑ በመሰረታዊ ሆነ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ የተጠናከረ የገበያ ጥናት ላይ የተመሠረተ ግብይት የማያደርግ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ቢሮዎች እና መምሪያዎች እንዲሁም ሸማች ማህበራት ከቀረቡ ጥያቄዎችና ከሰጡት ምላሽ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች በኮርፖሬሽኑ የስኳርና የፓልም ዘይት ስርጭት ወቅቱን ያልጠበቀ (የሚዘገይና የሚቆራረጥ) መሆኑን እንዲሁም በተቀመጠው ኮታ ልክ አገልግሎት እንደማያገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ለሸማቹ ህብረተሰብ ገበያን ለማረጋጋት ተብሎ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ የግል ነጋዴዎች ከሚያስመጡት (ከመርካቶ ዋጋ) ጋር ተመሳሳይ እና አንዳንድ ምርቶችም ከሌሎች አከፋፋዮች አንጻር ዋጋቸው ውድ የሆኑ ምርቶችን ለሽያጭ የሚያቀርብ መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በናሙና የተመረጡ ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ቢሮ እና መምሪያዎች፣ ቅርንጫፍ መደብሮች እንዲሁም ሸማች ማህበራት ስለጉዳዩ ተጠይቀው ገልጸዋል፡፡

71. በአዲስ አበባ ከተማ ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ወገን ለወገን ሸማች ማህበር የቀረበ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ከአለ በጅምላ ጋር በፊት ሸቀጥ የሚያስመጡ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ዘይት ብቻ የሚገዙ መሆኑ፤ የሸቀጥ መግዛት መቋረጡ ምክንያቱም ኮርፖሬሽኑ የሚሸጥላቸው ዋጋ ካሉት አከፋፋዮች አንጻር ውድ መሆኑ እና በተያያዥነት የማይፈልጉትን ዕቃዎች/ሸቀጦች ያለፍላጎታቸው እንዲገዙ መደረጉ ለምሳሌ የፕላስቲክ ለስላሳ መጠጦ፣ ሸኖለጋ ቅቤ እና የመሳሰሉት፤ ኮልጌት የጥርስ ሳሙና እነሱ ጋር ሲደርስ ጊዜው ያለፈበት መሆኑ፡፡ ዘይት በተፈቀደላቸው ኮታ ልክ የማይደርሳቸው መሆኑ (በወር 2 ጊዜ መውሰድ ሲገባቸው የማይወስዱ መሆኑን)፤

72. ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት ከኮርፖሬሽኑ በተሰጠ ምላሽ፤ ዘርፉ የገበያ ጥናት እያደረገ የሚሰራ መሆኑን፤ አንዳንድ ምርቶች ከሽያጭ መደብሮች ክምችት በአስቸኳይ መተካቱን፤ ነገር ግን አልፎ አልፎ መተካት የማይቻልበት ጊዜ መፈጠሩን፤

- አንደኛው አምራቹ የግብዐት እጥረት ሲያጋጥመው እና ምርቱ በጣም ተፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለኮርፖሬሽኑ ይልቅ ለግለሰቦች ለመሸጥ የመፈለግ አዝማሚያ በመኖሩ፡፡
- በተለይ ምርቶቻቸው ገበያ ላይ እስከሚለመድ ድረስ ከአለ በጅምላ ጋር መስራት የሚፈልጉ በርካታ አምራቾች መኖራቸው፤ ምርቱ ከተለመደላቸው በኋላ ግን ፍላጐታቸው ሲቀንስ መታየቱን፤ በተጨማሪም አለ በጅምላ የግል ባለሀብቱ እንደፈለገ ያደርገው የነበረውን ሸማች ለመከላከል የተመሰረተ ከመሆኑም አኳያ አምራቹም ይሁን አከፋፋዩ በበጐ የማየት ነገር አለመኖሩ፣

- በተጨማሪም አንዳንድ ምርቶች በሀገራችን ብቸኛ በመሆናቸው /እንደሌሎቹ ምርቶች አማራጭ የማይገኝላቸው/ በመሆኑ ህብረተሰቡ ላይ ተገቢ ያልሆነ ዋጋ እየጫኑበት መገኘቱን፣ ይህን አይነት ችግር ማስወገድ የሚቻለው ሌሎች ምርቶችን በአማራጭነት በማቅረብ መሆኑን፤ ከዚህ አኳያ ደንበኛው ያልለመደውን ምርት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲገዛ በሚነገረው ጊዜ የሚጠራጠር መሆኑን፤ ነገር ግን ከገዛው በኋላ ያንን ምርት ፈልጐ እንደሚመጣ፤ ከዚህ አኳያ ዘርፉ ያስለመዳቸው በርካታ ምርቶች ማቅረብ መቻሉን፡፡ በመሆኑም በአንድ አይነት ምርት ብቻ የተያዘውን ገበያ አማራጭ በማቅረብ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

73. ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን የዋጋ ጥናት ማካሄዱን የሚገልጽ ማስረጃ ቢያቀርብም በዋነኛነት የሚያገለግለውን የህብረተሰብ ክፍል አካባቢያዊ ሁኔታ ያገናዘበ የፍጆታ ዕቃዎች የፍላጎት ጥናት ማካሄዱን የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

74. ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰብ አካባቢያዊ ሁኔታ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት የማያካሂድ እና በወቅቱ ወደ ገበያ በመግባት በተመጣጣኝ ዋጋ የማያቀርብ ከሆነ ያለጥናት የሚገዙ ዕቃዎች ብልሽት እና ብክነት መቀነስ እንዲሁም እንደ ሀገር የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት ገበያ የማረጋጋት ድርሻ ለመወጣት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

### የሰው ኃይል አደረጃጀትና የስራ መዘርዝር በተመለከተ

75. ኮርፖሬሽኑ ለፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ዓላማውን ሊያሳካ የሚያስችል አደረጃጀት ሊያዘጋጅ፣ በተገቢው የሰው ኃይል ሊያሟላ እና የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

76. በዘርፍ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል 454 (ለ አንድ ቅርንጫፍ የተፈቀደው 48) ሲሆን በታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም በተገኘ መረጃ 274 ሰራተኞች የሚገኙ ሲሆን ከመረጃው ለመረዳት የሚቻለው 177 የሰው ኃይል ያልተቀጠረ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የሽያጭ መደብር ሃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ኮርፖሬሽኑ

- በዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ መደቦች ላይ (ለምሳሌ እንደ ዋና ገንዘብ ያዥ እና ገንዘብ ያዥ በዘርፉ ከሚያስፈልገው 35 የሰው ሃይል ውስጥ 17ቱ ያልተሟሉ መሆኑ፣
- የውስጥ መጋዘን ተቆጣጣሪ እንደ ዘርፍ ከሚያስፈልገው 7 የሰው ሃይል ውስጥ 2ቱን ያልተሟሉ መሆኑ፣
- የደንበኛ አገልግሎት ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ ላይ ከሚያስፈልገው 7 የሰው ሃይል ውስጥ 4ቱን ያላሟላ መሆኑ፣
- የደንበኛ አገልግሎት ባለሙያ የስራ መደብ ላይ ከሚያስፈልገው 14 የሰው ሃይል ውስጥ 4ቱን ያላሟላ መሆኑ፣
- የሽያጭ ተቆጣጣሪ መደብ ላይ ከሚያስፈልገው 49 የሰው ሃይል ውስጥ 22ቱን ያላሟላ መሆኑ፣
- እና የጥራት ቁጥጥር ሱፐርቫይዘር የስራ መደብ ላይ ከሚያስፈልገው 7 የሰው ሃይል ውስጥ 3ቱን ያላሟላ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

78. ስለጉዳዩ የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ዘርፉ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ከተዋሃደ በኋላ በውጪ አማካሪ በተጠናው የኮርፖሬሽኑ መዋቅር በአዲስ አደረጃጀት የተደራጀ መሆኑን ፤ በዚሁ መሠረት ሰራተኞች እንደ ሙያቸው ከሌሎች የኮርፖሬሽኑ የዘርፍ ሰራተኞች ጋር በመወዳደር በዚያው ዘርፍ ወይም በሌሎች የኮርፖሬሽኑ ዘርፎች እንዲመደቡ መደረጉን፣ በዘርፉ ከሚያስፈልገው 17 ገንዘብ ያዥ ውስጥ 13 መሟላቱን ገልጸው ለስራው የሚያስፈልገው የሰው ሃይል ብቻ የተመደበ ሲሆን የስራ መጠኑ እየጨመረ ሲሄድ በደረጃ እድገት ወይንም በሌሎች የምደባ ዘዴዎች የሚሟላ መሆኑን እና ይህ አካሄድ ሰራተኞችን ለማበረታታት ከመጥቀሙ ባሻገር የሰው ኃይል ብክነትንም ለመከላከል የሚያግዝ መሆኑን፣ እንዲሁም

79. ኮርፖሬሽኑ ለዘርፉ ሰራተኞች የሥራ መዘርዝር አዘጋጅቶ  የሰጠ መሆኑን፣ ነገር ግን አንዳንድ የሥራ መዘርዝሮች ላይ በማንኛውም አዲስ የተፈጠረ ተቋም እንደሚገጥመው በሥራ መዘርዝሩ ላይ ቢጨመሩ ወይንም ቢቀነሱ የሚል የሰራተኞች አስተያየት በተሰጠባቸው የሥራ መደቦች ላይ ጥናት አድርጎ ማስተካከያ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

80. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ይስጡ እንጂ በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ቅርንጫፍ መደብሮች የሰው ኃይል እጥረት መኖሩን እና ለሰራተኞች /ለባለሙያዎች የስራ መዘርዝር ተዘጋጅቶ ያልተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ በመቻሉ ለሰራተኞች ተሰጥቷል የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

81. ኮርፖሬሽኑ ለፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ዓላማውን ሊያሳካ የሚያስችል አደረጃጀት ካላዘጋጀ እና በተገቢው የሰው ኃይል  ካላሟላ እና ለሰራተኞች የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ካላደረገ  ሰራተኞች በከፍተኛ የስራ ጫና/ውጥረት ውስጥ እንዲሰሩ፣ ከማድረጉም በላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

### የቅሬታ አቀባበል የአሰራር ስርዓትን በተመለከተ

82. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

83. ኮርፖሬሽኑ የደንበኞች አስተያየት ቅሬታ አቀራረብና አቀባበል ስርዓት የሌለው መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች፣ በናሙና ከተመረጡ ቅርንጫፍ መደብሮች እና ሸማች ማህበራት በቀረበ ቃለ መጠየቅ በተሰጠ ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

84. ኮርፖሬሽኑ በዘርፉ ከምደባ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ቅሬታዎች ተገቢውንና  ቀጥተኛ የሆነ መልስ ለባህርዳር፣ ለሀዋሳ፣ ለመርካቶ እና ለቃሊቲ መደብሮች ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

85. የዘርፉ ኃላፊ ስለጉዳዩ በዝርዝር ኦዲት ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ከኮርፖሬሽኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ ዘርፉ በሁሉም ቅርንጫፎች የደንበኞች ሀሳብ መስጫ መዝገብ አዘጋጅቶ አሰራሩን ለማሻሻል  እየሰራ መሆኑ፣ በተጨማሪ ደግሞ በሻሸመኔ፣ ሀዋሳ፣ ደሴ፣ ባህርዳር እና አዲስ አበባ የሚገኙ ደንበኞቻቸው ጋር ውይይት እየተደረገ በአሰራር ላይ የሚታዩ ችግሮች እየተቀረፉ መሆኑንን ገልጸዋል፡፡

86. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ኮርፖሬሽኑ በዘርፉ የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን የሚገልጽና ቅሬታ አቅራቢው በቀላሉ የሚያቀርብበት ሂደት እንዴት፣ በምን አይነት ሁኔታና ለማን ቅሬታ ማቅረብ እንዲሚችል (ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቢሮ እና የመፍትሄ አሰጣጥ ሁኔታ) የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ እና እንደ ማስረጃ የቀረበው የደንበኞች ሀሳብ /አስተያየት መፍትሄን የማይገልጽ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

87. ኮርፖሬሽኑ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ካላደረገ ለሚያጋጥመው የአሰራር ስርዓት ችግር እና መሻሻል አዳጋች ይሆንበታል፡፡

## ዘመናዊ የመረጃ አያያዝን በተመለከተ

88. ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና መለዋወጫ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

89. ኮርፖሬሽኑ ለዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ የሚጠቀምበትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ውጤታማነቱን በየጊዜው እየገመገመ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል፡፡

90. ኮርፖሬሽኑ፣

- ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣ ለምሳሌ የግዥ፣ የክምችት እና የሽያጭ እንዲሁም የደንበኞች መረጃ ስለመኖራቸው በ ERP (Enterprise Resource Planning) Software የግዥ፣ ክምችት እና ሽያጭ መረጃ በወቅቱ ባለመመዝገቡ ወቅታዊ መረጃ እንዳይገኝ ያደረገ መሆኑን ግንዛቤ ስለተወሰደበት የሲስተም ኦዲት ግንቦት 1 2008 ዓ.ም በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (INSA) እንዲደረግለት ታቅዶ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፣

በኦዲት ወቅት ከተከለሱ መስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

91. በኦዲቱ በናሙና ከታዩ ቅርንጫፎች ለባህርዳር ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር ተ/ስራ አስኪያጅ ለቀረበ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ የመደብሩ ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች ዘርፉ ለዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ የሚጠቀምበት ERP በተባለው system

በቂ የአጠቃቀም ስልጠና ያልተሰጣቸው በመሆኑ የበለጠ በተሻለ መልኩ መጠቀም አለመቻላቸውን ግልጸዋል፡፡

92. በኦዲት ወቅት የዘርፉ የስራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ኮርፖሬሽኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ፣

- ዘርፉ Micro soft Daynamic Nav ERP የሚባል ቴክኖሎጂ የሚጠቀም መሆኑ፤
- ነገር ግን ይህ ቴክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ተደርጓል ማለት አለመቻሉ፤
- At Kerney የሚባል ዓለም አቀፍ አማካሪ በአማካሪነት ድርጅቱን ያቋቋመው ሲሆን ትግበራው ላይ ያጋጠሙት ችግሮች ድርጅቱን እስከ አሁን ህልውናውን እየተፈታተነው እንደሚገኝ ለምሳሌ ብዙ ብር ወጥቶበት የተገዛው Daynamic Nav ERP ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ባለመዋሉ ምክንያት የሽቀጥ ወጪ እና ገቢ መረጃ፣ የሂሳብ ሪፖርት በተገቢው መስራት አለመቻሉ
- ባለፈው አመት ያልተሰሩ ስራዎችን ኮሚቴ በማደራጀት ለማጥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑን

ገልጸዋል፡፡

93. ኮርፖሬሽኑ ለዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ Micro soft Daynamic Nav ERP የአሰራር ስርዓት በመገምገም ለችግሮቹ አፋጣኝ ማሻሻያ ካላደረገና ለተጠቃሚዎቹ ሥልጣነ ካልሰጠ፣ በዘርፉ የመረጃ አያያዝና የአሰራር ስርዓት ውጤታማነት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

### ንብረት አያያዝን በተመለከተ

94. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የንብረት አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. በኦዲቱ ወቅት በኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ስም ለአገልግሎት የተገዙ

- የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና ማጓጓዣዎች ለምሳሌ፡- Fork lift ፣ palyte hand terack፣ ICT Materials (laptop,printer & copy machine) ያለስራ ከሶስት ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆናቸው፤

- ለጀነሬተሮችና የዕቃ ማጓጓዣ ጋሪዎች ወቅታዊ ክትትልና ጥገና ያልተደረገ መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፤

96. በተጨማሪም የዘርፉ ተሽከርካሪዎች ያለምንም ስራ እስከ 18 ቀን ድረስ የሚቆሙ ሲሆን በእነዚህም ቀናት ዘርፉ እነዚህን መኪኖች መጠቀም ሲገባው በኪራይ መኪኖችን በማስገባት የሚጠቀም መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ የመርካቶ እና የባህርዳር ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር ኃላፊዎች ለቀረበ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ፣

  - ኮርፖሬሽኑ/ዘርፉ የሚያስፈልጉ ንብረቶች በወቅቱ የማቅረብ፣ በጥንቃቄ መያዙን እና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በዓመት አንድ ጊዜ ከሚደረግ ቆጠራ በስተቀር የክትትል እና የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፣

- የገንዘብ መቁጠሪያ ማሽን በተደጋጋሚ እንዲገዛላቸው ቢጠይቁም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣ ኮርፖሬሽን ከመሆኑ በፊት በየ 15 ቀን ውስጥ የንብረት አጠቃቀምና ያጋጠሙ ችግሮችን በተመለከተ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረግ እንደነበር፤ ኮርፖሬሽን ከሆነ በኋላ በአመት አንድ ጊዜ ከሚካሄድ የንብረት ቆጠራ ውጪ ሌላ የንብረት የአፈጻጸም ግምገማ፣ የክትትል እና የቁጥጥር ስራ እየተሰራ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

98. የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ አንዳንድ ማሽኖች በተደጋጋሚ በመጠገናቸው ምክንያት አገልግሎት ለመስጠት የማይችሉ በመሆናቸው መተካት እንደሚኖርባቸው፤ ነገር ግን ከካፒታል እጥረት ጋር በሚነሳው ችግር ምክንያት ይህንን ማድረግ አለመቻሉ፤ ፎርክሊፍቶችን በተመለከተ መለዋወጫ ዕቃ በአቅራቢው ብቻ የሚገኝ በመሆኑ እና አቅራቢው ደግሞ በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ዕቃዎችን ማስገባት እንዳልቻለ ገልጸዋል፡፡

99. የፓሌት ማዘዋወሪያ ጋሪዎች ጥገና ስራ ከፋሲል መኮንን ጋራጅ ጋር ጊዜያዊ ውል የተገባ መሆኑን በረቂቅ ሪፖርት ከኮርፖሬሽኑ በማስረጃ የተደገፈ ምላሽ ተሰቷል፡፡

100. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የንብረት አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ የማያደርግ ከሆነ ለዘርፉ ስራ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን አዳጋች ያደርገዋል ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

101. በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፣

- ኮርፖሬሽኑ ከቀድሞው አለ በጅምላ ከመጣ ብድር የተነሳ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ውስጥ መሆኑ እና ከፍተኛ ዕዳና ወለድ እየከፈለ የሚገኝ መሆኑ እና ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመስራት ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን ግዥ በዋጋ ማቅረቢያ ብቻ የሚፈጽም መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ የፓልም የምግብ ዘይት ግዥን በገበያ ጥናት መሠረት እየፈጸመ አለመሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ዋጋን እንጂ ጥራትን መሠረት የማያደርግ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ አብዛኛውን የአገሪቱን አካባቢ እና ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ ያመጣቸውን ዕቃዎች በወቅቱ ከወደብ ስለማያነሳ//ዕቃዉን ጭነው ሳያራግፉ በግቢ ውስጥ በመቆየታቸው አላስፈላጊ የሆኑ የመጋዘን እና የዲሜሬጅ ክፍያዎች የተከፈሉ መሆኑ፣
- በኮርፖሬሽኑ ሳይወገዱ የቆዩ የተጎዱና የተበላሹ ጊዜ ያለፈባቸው የፍጆታ ዕቃዎች መኖራቸው፣
- ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና (minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን ፍላጎትና የገበያውን ሁኔታ መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት የማያካሂድ መሆኑ፣

- ለፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ሰራተኞች /ለባለሙያዎች የስራ መዘርዝር (Job Description) ተዘጋጅቶ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሰው ኃይል እጥረት ያለበት መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ ለዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ Micro soft Daynamic Nav ERP የአሰራር ስርዓት በመገምገም ለችግሮቹ አፋጣኝ ማሻሻያ ያላደረገ መሆኑ፣
- ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ሀሳብ/ አስተያየት መቀበል ብቻ ሳይሆን ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቢሮ እና የመፍትሄ አሰጣጥ ሁኔታ የሚገልጽ የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፣
- ሳይጠገኑ ተበላሽተው የተቀመጡ ንብረቶች መኖራቸው፣

ታውቋል፡፡

ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

102. በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅት በመፍጠር የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ /አለ በጅምላ/ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ያከናውን ዘንድ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ከመቀላቀሉ በፊት የነበረው ሂሳብ ተዘግቶ ኦዲት ሊደረግ ይባል፡፡ ከ2008 እስከ 2010 በጀት ዓመት ዓመታዊ ሒሳብ እንዲዘጋ ሊያደርግ ይገባል፣
- የቀድሞው አለ በጅምላ ሲቋቋም ከባንክ የተበደረው ብድር በታህሳስ 2008 ዓ.ም. ወደ ኮርፖሬሽኑ ሲቀላቀል የብድሩ ዋናው (principal) ክፍያ እፎይታ ጊዜው በሦስት (3) ዓመት በመጠናቀቁ እ.ኤ.አ ከመስከረም 2016 ጀምሮ ዕዳና ወለድ በየሶስት (3) ወሩ ብር ወደ 21 ሚሊዮን (በዓመት 84 ሚሊዮን) ኮርፖሬሽኑ እየከፈለ በመሆኑና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥና ሽያጭ ለማከናወን በየቀኑ በተመሳሳይ ወለድ ምጣኔ የሚታሰብበት ከ100 - 235 ሚሊዮን በሚደርስ " Negative Over Draft Facility" በብድር በመሆኑ ይህ ኮርፖሬሽኑ የተቋቋበትን አላማ ለማሳካት እንቅፋት በመሆኑ በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እና የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ችግሩ የሚቀረፍበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- በኮርፖሬሽኑ የሚከናወኑ ግዥዎች ግልጽነትና ፍትሃዊነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለበት በስተቀር የፍጆታ ዕቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ ግዥ መፈጸም ይኖርበታል፣ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት የነበረ ልምድ ተብሎ በኮርፖሬሽኑ እየተከናወነ ያለው የፓልም የምግብ ዘይት ግዥ የሚከናወንበት መንገድ በጥናት ተከልሶ ሂደቱ ሊስተካከል ይገባል፡፡ ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ዋጋን ብቻ ሳይሆን ጥራትን (የህብረተሰብ ጤናንና ደህንነትን ከግምት ያስገባ) ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ኮርፖሬሽኑ የሚያከናውናቸው የዕቃ ግዢዎች የአገልግሎት መቆያ ጊዜ ቢያንስ ምን ያህል መሆን እንዳለበት በግልጽ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ ይህንንም በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ያልተቋረጠ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ የሚበላሹ ጊዜ የሚያልፋቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ሊቀንስ/እንዳይኖሩ የሚያደርግ አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተለያየ ምክንያት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የደረሰና ያለፈ ለገበያ ሊቀርቡ የማይችሉ እቃዎችን በኮርፖሬሽኑ በተቀመጠው አሰራር መሠረት ሊያስወግድ ይገባል፤፡
- ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛና (minimum stock level) ከፍተኛ (Maximum stock unit) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣
- ኮርፖሬሽኑ የህብረተሰቡን እና የገበያውን ሁኔታ ለመረዳትና ተፈላጊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችን ለማቅረብ የሚያስችል የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፣ የሚከናወነው ጥናትም ለስትራቴጂክ ዕቅድ እንደግብዓት ሊያገለግል ይገባል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት አላማን ለማሳካትና በሁሉም አካባቢዎች ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት በመዘርጋትና ከዚህ በፊት በጥናት የተለዩትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ማቆያ መጋዘኖች እና መሸጫ መደብሮች ሊያስፋፋ ይገባል፤፡
- ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ዓላማን ለማሳካት እንዲረዳው የተፈቀዱ የሥራ መደቦችን በተፈላጊው የሰው ኃይል ሊያሞላ እና ለሁሉም ሰራተኞች /ለባለሙያዎች/ የስራ መዘርዝር (Job Description) ተዘጋጅቶ እንዲሰጥና ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት አሰራር ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፣
- ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሚጠቀምበትን ቴክኖሎጂ Micro soft Daynamic Nav ERP የአሰራር ስርዓት በመገምገም ችግሮችን በመቅረፍ ቴክኖሎጂውን በሙሉ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡

- ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ግልጽ እና መፍትሄ ተኮር የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ኮርፖሬሽኑ በዋናው መ/ቤትም ሆነ በተለያዩ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ተበላሽተው የሚገኙ ንብረቶች በፍጥነት ተጠግነው ለሥራ የሚውሉበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡ ተጠግነው በሥራ ላይ የማይውሉትን ህግን በጠበቀ ሁኔታ የሚወገዱበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

103. በመጨረሻም የኮርፖሬሽኑ፣ የዘርፉ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ በናሙና ባየናቸው ቅርንጫፍ መደብሮች፣ ንግድ መምሪያና ቢሮዎች እና ሸማች የህብረት ስራ ማህበራት በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የስራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

## አባሪ 1፡ በናሙና የታዩ

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት  ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ቢሮ
2. የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት መምሪያ
3. በባህርዳ ከተማ ሹማቦ ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
4. በባህርዳር ከተማ  በላይ ዘለቀ ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
5. በባህርዳር ከተማ  ግሽ አባይ  ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
6. በባህርዳር ከተማ  አለ በጅምላ ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር
7. በሀዋሳ  ከተማ  አለ በጅምላ ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር
8. በአዲስ አበባ ከተማ መርካቶ አለ በጅምላ ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር
9. በአዲስ አበባ ከተማ ቃሊቲ አለ በጅምላ ቅርንጫፍ መሸጫ መደብር እና መጋዘን
10. በአዲስ አበባ  ከተማ አንድነት ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
11. በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 15/16 ወገን ለወገን ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
12. የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ቢሮ
13. በሀዋሳ ከተማ ራስ አገዝ ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
14. በሀዋሳ ከተማ ሰፈረ ሰላም ሸማች ህብረት ስራ ማህበር
15. በሀዋሳ ከተማ ቁምነገር ሸማች ህብረት ስራ ማህበር

## አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| 1. ኮርፖሬሽኑ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የፍጆታ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር በመግዛት የሀገር ውስጥ ገበያን ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፡፡ | 2. ኮርፖሬሽኑ መሰረታዊ ሸቀጦችን የሚለይበት መስፈርት አዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ደንብ ቁጥር 369/2008 አንቀጽ 5/1 |
| | 3. ኮርፖሬሽኑ ዘርፉ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራን በሚመለከት የረዥም ጊዜ /strategic/ ፣ የመካከለኛው ዘመን/middle term/ ፣ የዓመት /operational/ ፣ የመንፈቅ እና የሩብ ዓመት ዕቅድና ሪፖርት እንዲያዘጋጅ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ:-መልካም ተሞክሮ |
| | 4. ኮርፖሬሽኑ ለፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ ዓላማውን ሊያሳካ የሚችል አደረጃጀት ሊያዘጋጅ እና በተገቢው የሰው ኃይል ሊያሟላ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ መልካም ተሞክሮ |
| | 5. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የሰራተኞች የስራ መዘርዝር (Job Description) አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣መልካም ተሞክሮ |
| | 6. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ የስራ ሂደት መግለጫ /Process Description/ ወይም የተለያዩ የሥራ ክፍሎች የስራ ሂደት ፍሰት ዝርዝር መግለጫ አዘጋጅቶ እንዲይዝ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣መልካም ተሞክሮ |
| | 7. ኮርፖሬሽኑ በዋነኛነት የሚያገለግለውን የህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብቁጥር |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 369/2008 ፤ የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 52 |
| | 8. ኮርፖሬሽኑ ዓመታዊ የፍጆታ ዕቃዎች የግዥ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በሚመለከተው አካል ሊያፀድቅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 106፤ የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 9. ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ግገር ዕቅድ ግዥዎች የሚገዙበትን የግዥ ዘዴ በግልጽ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 52-55፤ የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 10.ኮርፖሬሽኑ የሚፈጽማቸውን የፍጆታ ዕቃ ግዥዎች አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር በግልፅ ጨረታ ሊያከናውን ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡ የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ16፣ 52-55 ፤የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም አዋጅ 649/2001 |
| | 11.ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ መርምሮ የሚያፀድቅ የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 52-55፣ 106፤የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 12.በኮርፖሬሽኑ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ለሚፈጸም ግዥ ድርድር የማድረጊያ አትኩረት- ነጥቦች ዝርዝር በኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ ፀድቆ ለተደራዳሪዎች ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግገር ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 53-55፤ የፌደራል መንግስት የግዥ አዋጁ 649/2001 አንቀጽ 52/2 |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 13.ኮርፖሬሽኑ ለሚገዛቸው የፍጆታ ዕቃዎች ምርት ትክክለኛ የሆነ የጥራት ደረጃ (Standard) እንዲወጣላቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዢ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 52 |
| | 14.የኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ አፈፃፀም ሂደት በፀደቀው የግዥ እቅድ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ ምንጭ፡ የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 15.ኮርፖሬሽኑ የሚገዛቸው የፍጆታ ዕቃዎች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት(Specification) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ምንጭ፡ የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የእህል የቡና የአትክልት ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዢ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 52 ፣ የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 16.ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃ በመረከቢያ ሠነድ ተሞልቶ ገቢ ከመደረጉ በፊት ዕቃው/ሽቀጡ የተጠየቀውን መስፈርት ማሟላቱን በሚመለከተው ባለሙያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የእህል፣የቡና፣ የአትክልት፣ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ክምችት፣ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገፅ 87 |
| 2. ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን በዘመናዊ ሽያጭ ማዕከሎቹ በማከማቸት ከግሉ የንግድ ዘርፍ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር | 17.ኮርፖሬሽኑ ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ገዝቶ የሚያስመጣቸውን የፍጆታ ዕቃዎች ደረጃውን ጠብቆ በተገነባ መጋዘን ዉስጥ እንዲከማች ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-በምግብ ላኪ፣ አስመጪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 32/2009 ፣የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፣የእህል/የቡና ፣ የአትክልት ፣ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት Evaluative Criteria |
|---|---|
| በመተባበር ፤ በቀጥታና በቸርቻሪዎች አማካኝነት ለተጠቃሚ በማድረስ በሀገሪቱ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈ፣ አሰራርና ውድድር ላይ የተመሠረተ የግብይት ስርዓት በማጠናከር የሀገር ውስጥ ገበያን ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፡፡<br>2.1ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈ፣ ውጤታማ የገበያ ማረጋጋት ሥራ ለመስራት የሚያስችለውን የፍጆታ ዕቃዎችን በዘመናዊ ሽያጭ ማዕከሎቹ የህብረተሰቡን/የተጠቃሚዉን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ክምችት የያዘ መሆኑን መገምገም፡፡ | 18.ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ ያሉ ከምግብ ነክ ምርቶች ጋር ንክኪ ያላቸው ሰራተኞችን / Food Handlers በየ ስድስት /6/ ወሩ የጤና ምርመራን እንዲያደርጉ ሊያደረግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ በምግብ ላኪ፣ አስመጪና አከፋፋይ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 32/2009 ፤በጥራት መምሪያ የልማት ቡድን አባላት የተደረገ ውይይት- ቃለ-ጉባኤ 07/04/09 ገጽ 4 |
| | 19.ኮርፖሬሽኑ የሚሰራጩ የፍጆታ ሸቀጦች የተበላሹ እና የጎደሉ ካሉ ተለይተው እና ተቆጥረው ወይም ተመዝነው ለየብቻ እንዲቀመጡ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የእህል/የቡና ፤ የአትክልት ፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 148 |
| | 20.ኮርፖሬሽኑ በተበላሹ እና በጎደሉ የፍጆታ ሸቀጦች በውል መሰረት የሚተኩ ካሉ እንዲተኩ ሊያደርግ ይገባል ፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የእህል/የቡና ፤ የአትክልት ፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 148 |
| | 21. ኮርፖሬሽኑ ለእያንዳንዱ የፍጆታ ምርት አይነት (store keeping unit) አነስተኛ (Minimum Stock Level) ና ከፍተኛ(Maximum Stock Level) የምርት ክምችት መጠን ወስኖ ተግባራዊ ሊደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የእህል/የቡና ፤ የአትክልት ፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 110 |
| | 22.ኮርፖሬሽኑ ከውጭ አገር ተገዝተው ለሚገቡ ምርቶች ለሶስት ወር የገበያ ፍላጎት የሚሆን ምርት ሊይዝ ይገባል ፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የእህል/የቡና ፤ የአትክልት ፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 110 |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| 2.2. ኮርፖሬሽኑ ከግሉ የንግድ ዘርፍ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ፤ በቀጥታና በቸርቻሪዎች አማካኝነት የፍጆታ ዕቃዎችን ለተጠቃሚ በማድረስ በሀገሪቱ ዘመናዊ፣የተቀላጠፈ፣ አሰራርና ውድድር ላይ የተመሠረተ የግብይት ስርዓት በማጠናከር የሀገር ውስጥ ገበያን ውጤታማ በሆነ መልኩ እያረጋጋ መሆኑን መገምገም፡፡ | 23.ኮፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎች የስርጭት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በማጥናት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ሐምሌ 16 /2009 ገጽ 4 |
| | 24.ኮርፖሬሽኑ እጥረት ያለባቸውን የፍጆታ ሸቀጦችን በወቅቱ ወደ ገበያ በመግባት በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን ሊያረጋጋ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የ እህል/የቡና ፣ የአትክልት ፣ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 52-53 |
| | 25.ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን/ምርቶችን ለተጠቃሚዎች የሚያደርሱ ቸርቻሪ ነጋዴዎችን የሚመርጥበት መስፈርት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፣መልካም ተሞክሮ |
| | 26.ኮርፖሬሽኑ የፍጆታ ዕቃዎችን/ምርቶችን በተወዳዳሪ ዋጋ በቸርቻሪዎች አማካኝነት ለተጠቃሚው እንዲደርስ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ(2009-2012) *ገጽ 13* |
| | 27.ኮርፖሬሽኑ በየጊዜው የፍጆታ ዕቃዎች የገበያ ዋጋ ጥናት /market intelligence/ በማካሄድ ፤በወቅቱ ያለውን ትክክለኛ መረጃ በመያዝ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያሰራጭ እና የገበያ የማረጋጋት ስራን ሊሰራ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የ እህል/የቡና ፣ የአትክልት ፣ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም) ገጽ 126 |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | 28.በኮርፖሬሽኑ ገበያን ለማረጋጋት የሚሰራጩ ሸቀጦችን ላልተፈለገ ዓላማ በሚያውሉ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የ2010 ግማሽ በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የካቲት 30/2010 ዓ.ም ገጽ 33 |
| | 29.ኮርፖሬሽኑ የሚሰራጩ የፍጆታ ዕቃዎች መጀመሪያ የገባው መጀመሪያ ይወጣል (FIFO) የሚለውን የሒሳብ አሠራር መሠረት ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ፤የ እህል/የቡና ፤ የአትክልት ፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ ክምችት ስርጭትና ሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ገጽ 148 |
| | 30.ኮርፖሬሽኑ የተቀላጠፈና በዘመናዊ የፍጆታ ዕቃዎች ሽያጭ ሁሉንም ህብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ(2009-2012) *ገጽ 13* |
| | 31.ኮርፖሬሽኑ የገበያ ማረጋጋት ሥራን ለማከናወን የሚረዳው የግብይት ስልቶችን /Marketing Strategy/ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤ መጋቢት 15 እና 16/2009ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ የሰጡት አስተያየት ግብረ መልስ ለማማኔጅመንት ውይይት የቀረበ ገጽ 2 ፤ በጥራት መምሪያ የልማት ቡድን አባላት የተደረገ የመጀመሪያ ውይይት- ቃለ-ጉባኤ 25/02/09 ገጽ 4 |
| 3.ኮርፖሬሽኑ በውስጡ ካሉ ሌሎች ዘርፎች ፤ ከግሉ የንግድ ዘርፍ፤ከማህበራት/ከተጠቃሚ | 32.ኮርፖሬሽኑ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና መለዋወጫ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት (ጳጉሜ 2008) ገጽ 47 |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| ው እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የተዘረጋ መሆኑን፤ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ እና ቀልጣፋ አገልግሎት እየሠጠ መሆኑን መገምገም፡፡ | 33.ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ሥራ ዘርፍ ግብይት ለማሻሻል ጥናት በማከናወን አሰራሩን ሊያሻሽል ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008 ፤ የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ(2009-2012) ገጽ 13 |
| | 34.ኮርፖሬሽኑ ለዘመናዊ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ የሚጠቀምበትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ውጤታማነቱን በየጊዜው እየገመገመ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የማኔጅመንት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 06 ግንቦት1/2008 ዓ. ም ገጽ 3-4 |
| | 35.ኮርፖሬሽኑ በፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የደንበኞች የቅሬታ መቀበያ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ሐምሌ 16 /2009 ገጽ 4 |
| | 36.ኮርፖሬሽኑ የንብረት አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የኮርፖሬሽኑ የፋይናንስ ስራ አመራርና አሠራር መመሪያ ክፍል ዘጠኝ/9/፤ ከየፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም አዋጅ ቁ. 649/2001 |
| | 37.ኮርፖሬሽኑ የተከናወኑ የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ ፣ ክምችት ፣ ስርጭትን የሽያጭ አፈጻጸምን የሚገልጽ ሪፖርት ቢያንስ በየሶስት ወሩ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሊያቀርብ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የእህል፤የቡና፤ የአትክልት፤ ፍራፍሬና የፍጆታ ዕቃዎች ግዥ፣ክምችት፣ስርጭትና ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ገጽ 13 |
| | 38.ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ በዘመናዊ አሰራርና ውድድር ላይ የተመሰረተ የፍጆታ ዕቃዎች የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ስርዓት እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው የመንግስትና የግል አካላት ጋር በትብብር ሊሰራ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| | ምንጭ፡-የኢትዮጵያ የንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 369/2008፤የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ(2009-2012) ገጽ 13 |
| | 39.ኮርፖሬሽኑ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የምክክር መድረክ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ መልካም ተሞክሮ |

Office of the Federal Auditor General

# አባሪ 3፡ የፍጆታ ዕቃዎች ንግድ ስራ ዘርፍ/ አለ በጅምላ/ድርጅታዊ መዋቅር

